# የወንድም ከሓዲ!

ከባዕድ፣ ከጠላት የተስማሙ ሁሉ
ለዴሞክራሲና ለዕድገት እያሉ
በሓሰት ወገንን ሁሌ እያታልሉ
ኣሜሪካን ጭምር በተንኮል ደለሉ!
        ለባዕድ መንግሥታት እያሳበቁባት
        የገዛ ልጆቿ ጠላቶች ሆኑባት…

“ልጆቼ!” እያለች ኣብልታ፣ ኣጠጥታ
ያሳደገቻቸው ኣስተምራ፣ ቀጥታ
“ኣትስጧት ኢትዮጵያን ትከልከል እርዳታ
እጆቿን እሰሩ፣ ዕድገቷም ይገታ…”
        የሚሉ ምሁራን የዛሬ ልጆች
        ኣረ ከየት መጡ እኒህ ውርጋጦች?

ከጠላት ተግባብተው እንደ እጅ ሹራብ
“ብድርም ከልክሏት፣ ድሃውም ይራብ”
እያሉ ፉከራ፣ ቀልድና፣ ተረብ፣
ኢትዮጵያን ለማጥፋት በተንኰል ዓረብ
ሲጠቀምባቸው፣ ጉድ በሉ፣ ዓጀብ!
        ጠላት በእጅ-ኣዙር ከከሓዲዎች ጋ-
        በሃገራችን ላይ መረቡን ዘረጋ!

የሃገርን ጉዳይ በባዕዶች ሸንጎ
የጠላቶችም እጅ ኣንዲገባ ሰርጎ
ትችቱም ተጽፎ እንዲወጣ ኣድርጎ
በሽንገላ ቋንቋ ሸፋንፍኖ በእርጎ
        የሚጥር የሃገር ልጅ ከሓዲና ጎጂ
        ነውና ቅጣቱ ይከፈለው እንጂ!

ገ/ኢ. ጐርፉ።